# «መሬት ላራሹ!» . . . መሬት የለሹ

ይሸነሸናል፥ ይቆራረሳል፥ ይቸረቸራል . . . መሬት። የኢትዮጵያ መሬት። የኢትዮጵያ ምርጥ የእርሻ መሬት። በአዋጅ፥ በይፋ፥ በጠራራ ፀሐይ . . .

«ገንዘብ ያለህ ሁሉ የውጭ ዜጋ፥ የውጭ ኩባንያ፥ የውጭ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ፈጥነህ ና! በገንዘብህ የፈለግኸውን የኢትዮጵያን መሬት ግዛ! የፈለግኸውንም አምርተህ ወዳገርህ ስደድ! ድርሻህ የሆነውን የኢትዮጵያን መሬት አሁኑኑ በገንዘብህ ውሰድ! ና! በኢትዮጵያ መሬት፥ በኢትዮጵያ አፈር የየራስህን ሕዝብ አጥግብ። ምርጥ የሆነውንም መሬት ለራስህ መርጠህ ሙሉ የባለቤትነት መብትህን በኢትዮጵያ ምድር ላይ አረጋግጥ። ብቻ ገንዘብህን ይዘህ ና! ኢትዮጵያን ተጫረት! ኢትዮጵያ የትውልድ አገርህ ባትሆንም ዶላር እስከከፈልክ ድረስ የተንጣለለው የእርሻ መሬት ያንተ ነው! ና! በቅናሽ ዋጋ ኢትዮጵያን ግዛ! ና!» . . .

ዛሬ በኢትዮጵያ መንግሥት ብርቱ ትጋት በመካሄድ ላይ ያለውን ይህንን የመሬት ችርቻሮ ንግድ በተመለከተ ሰሞኑን በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ወጥቶ የነበረ የዜና ሐተታ ነው ለዚህ ጽሑፌ መነሻ የሆነኝ። በአሜሪካ አሉ ከተባሉት ታላላቅ፥ ታዋቂና ተአማኒ ጋዜጦች አንዱ በሆነው በዚህ ጋዜጣ ፊት ለፊት ገጽ ላይ በዐብይ ዘገባነት ሰፊ ዓምድ ተሰጥቶት የታተመው «ዜና» የማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ልብ በሀዘን የሚሞላ፥ በሀፍረትም የሚያሸማቅቅ ቢሆን አይደንቀኝም . . . ለእኔ የተሰማኝን ሀዘንና ሀፍረት አውቀዋለሁና። ከዋናው የዜና ርዕስ ከፍ ብሎ በትልቁ የታተመው ባለቀለም ፎቶግራፍ አምስት ኢትዮጵያውያን በበቆሎ እርሻ ውስጥ ጎንበስ ብለውና አንገታቸውን አቀርቅረው፥ በሥራ ተጠምደውም ያሳያል። ኢትዮጵያውያኑ በአገራቸው መሬት ላይ ላባቸውን ማፍሰሳቸው፥ ጉልበታቸውን መከስከሳቸው በእጅጉ ቢያስደስት እንጂ አያስከፋም። የለም! የሚያስከፋው፥ የሚያሳዝነውና በሀፍረት የሚያሸማቅቀው ከፎቶግራፉ ስር የተቀመጠው መግለጫ ነው። በፎቶግራፉ ላይ የሚታዩትና የማይታዩትም ሌሎች አያሌ ኢትዮጵያውያን የመሬቱ ባለቤት በሆኑት ሕንዳውያን አለቆቻቸው የበላይ ተቆጣጣሪነት ወደ ሕንድ አገር የሚላክ ምርት የሚያመርቱ፥ በገዛ አገራቸው መሬት ላይ ያመረቱትን እህል መብላት የማይችሉ የኪራይ ገበሬዎች መሆናቸው በእርግጥም ያስከፋል፥ ያሳዝናል፥ ያሳፍራል።

ጋዜጣው ላይ ከታተመው የዜናው ዋና ርዕስ ስር ጎላ ብሎ የተቀመጠው ንዑስ ርዕስ እንደሚከተለው ይነበባል፤

**Lured by a new business model, wealthy nations flock to farmland in Ethiopia, locking in food supplies grown half a world away**[*]

በሰፊው እርሻ ላይ የሚመረተው ምርት ሙሉ በሙሉ ወደ ሕንድ አገር ተልኮ የሕንድን ሕዝብ እንዲመግብ ነው ለም የሆነውን የኢትዮጵያ መሬት ሕንዳውያኑ በባለቤትነት የያዙት። የራሷ ልጆች በምግብ እጦት እየረገፉ ለም መሬቷን፥ ወርቅ አፈሯን ለሌሎች አሳልፋ የምትሰጥ፥ ለሌሎች በርካሽ የምትቸበችብ አገር ሆናለች

[*] "The ultimate crop rotation" by Stephanie McCrummen; *The Washington Post*; Monday, November 23, 2009; Pages A1 & A12.

የዛሬዋ ኢትዮጵያ። ወንዞቿ ድንበሮቿን አቋርጠው ሌሎችን ማበልጸጋቸው ሳያንሳት መሬቷን ለዶላር የሚቸበችብ መንግሥት «እባካችሁ ኑ! ኢትዮጵያን ግዙ!» በሚል የግብዣ ጥሪ ለውጭ አገር ዜጎች፥ መንግሥታትና አትራፊዎች ያለምንም ይሉኝታ እየሸጣት ይገኛል (አሁንም ከጋዜጣው ጥቂት ቃላት ልዋስ)፤

**In recent months, the Ethiopian government began marketing abroad one of the hottest commodities in an increasingly crowded and hungry world: farmland. "Why attractive?" reads one glossy poster with photos of green fields and a map outlining swaths of the country available at bargain-basement prices. "Vast, fertile, irrigable land . . . . Abundant water resources. Cheap labor. Warmest hospitality."**

የራሷ ዜጎች ከአንዱ የአገራቸው ክፍል ወደሌላው ሄደው የመኖር፥ የመሥራት፥ ቤትና ንብረት የመገንባት መብትም አቅምም ተነፍጓቸው በድህነትና በረሀብ ሲሰቃዩ፥ በአንጻሩ ግን ገንዘብ የመክፈል አቅም ያለው ማንኛውም የውጭ ዜጋ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል በነጻነት እየተዘዋወረና እየተንሸራሸረ፥ ከአውሮፕላን ላይ ሆኖ ለዐይኑ የሚያስደስተውንና ልቡ የተመኘውን የእርሻ መሬት በፈለገው መጠን በባለቤትነት የመያዝ መብቱ የተረጋገጠባት አገር ሆናለች። ጋዜጣው ይህንን እውነታ እንደሚከተለው አስቀምጦታል፤

**Lured with 40-year leases and tax holidays, investors are going on farm shopping sprees, crisscrossing the country on chartered flights to pick out their swaths of Ethiopian soil.**

በድህነታችንና ረሀብተኞች በመሆናችን ብዙ ጊዜ ሲያዝንልን፥ አንዳንዴም ሲሳለቅብን የኖረው ዓለም፥ አሁን ደግሞ የራሱን ሕዝብ እያስራበ ለውጭ አገሮች ምግብ ፍጆታ እንዲውል ለም የሆነውን የአገሪቱን የእርሻ መሬት የሚሸጥ መንግሥት እንደተሸከምን ሲያውቅ ምን ስም እንደሚሰጠን ለመገመት እቸገራለሁ። አሁንም ጋዜጣው ስለኢትዮጵያ ያሰፈረውን ሌላ ቁምነገር ልጥቀስ፤

**This impoverished and chronically food-insecure Horn of Africa nation is rapidly becoming one of the world's leading destinations for the booming business of land leasing, by which relatively rich countries and investment firms are securing 40-to-99-year contracts to farm vast tracts of land. . . . Few countries have embraced the trend as zealously as Ethiopia . . . .**

ይህንን ጋዜጣዊ ዘገባ ሳነብ የኢትዮጵያን ድንበር ለቀው ከመሄዳቸው ወይም ደግሞ መርከብ ላይ ከመሳፈራቸው በፊት በንጉሥ ትእዛዝ እግራቸውንና ጫማቸውን በኢትዮጵያ ውሃ እንዲታጠቡ የተደረጉት ፈረንጆች ጉዳይ ትዝ አለኝ . . . የኢትዮጵያን አፈር በጫማቸው ይዘው እንዳይሄዱ፥ የኢትዮጵያን አፈር ወደሌላ አገር እንዳያሸሹ ሲባል «በእግሮቻችሁ የያዛችሁትን የኢትዮጵያ አቧራ አራግፉና

ሂዱ» የተባሉት እነዚያ ግራ የተጋቡት ነገር ግን እንደታዘዙት አፈሯን፥ አቧራዋን ከየእግሮቻቸው አራግፈው የሄዱት ፈረንጆች። ድሮ ነው ይሄ ታሪክ የተፈጸመው ታዲያ . . . ለኢትዮጵያ አፈር፥ ለኢትዮጵያ ክብርና አንድነት የሚንገበገቡ፥ የሚነዱ፥ የሚቃጠሉ መሪዎች በነበሩበት ዘመን። ለነጻነትና ለአንድነት በጽናት መቆም ባልረከሰበት ዘመን።

ዛሬማ . . . ማን ለ«አፈታሪክ» ጊዜ አለው? ዘመኑ የ«ግሎባላይዜሽን» ዘመን ስለሆነ ሌላው ዓለም እንደሆነው መሆን ሥልጣኔ እንጂ ጥፋት አይደለም፤ ነው እንዴ? በፍጹም! «የሠለጠነው» ዓለም ለገንዘብ ነፍሱን፥ ሕሊናውንና ክብሩን የሚሸጥ ከሆነ እኛም ነፍሳችንን፥ ሕሊናችንንና ክብራችንን ብንሸጥ ምናለበት? ምንም! . . . ይህንን አደገኛ አመለካከት ነው የዛሬውን የኢትዮጵያን መንግሥት የሚመሩት ሰዎችና ደጋፊዎቻቸው የሚያራምዱት። ኢትዮጵያ ብትቆራረስ፥ ብትሸጥ፥ ብትቆስል፥ ብትደማ በማንኛውም መልኩ «ፎሪን ከረንሲ» እስካስገኘች ድረስ መቆራረሷ፥ መሸጧ፥ መቁሰሏ፥ መድማቷ ጉዳያችን አይደለም የሚሉ «መሪዎች» የበቀሉበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ለ40 እና ለ99 ዓመታት ለም የሆነውን መሬታችንን ለሌሎች በኮንትራት ማስረከባችን ጉዳቱ ያልታያቸው፥ ወይም ደግሞ ኢትዮጵያን የመገንባት ሳይሆን የማፍረስ ሱስ የተጠናወታቸው «አዋቂዎች» ምን ዓይነት ኢትዮጵያ ለትውልድ እንደሚያስተላልፉ ለማሰብ ያስቸግራል። በዐይናችን እያየን አገር እንደተራ ሸቀጥ ተቸርችራ ሳታልቅ «ምን እየሆንን ነው?» የሚለውን ጥያቄ ራሳችንን ለመጠየቅ ብንዘጋጅ መልካም ነው . . . ከእርስበርስ ንትርክ፥ ተለያይቶ ከመዳከም፥ ለራስ ጥቅም ሲሉ ዓላማን ከመካድና በአሉባልታ ከመጠመድ ፋታ ካገኘን! ወደጋዜጣው ዘገባ ልመለስ፤

> **The scale and pace of the land scramble have alarmed policy-makers and others concerned about the implications for food security in countries such as Ethiopia, where officials recently appealed for food aid for about 6 million people as drought devastates parts of East Africa.**

«የኢትዮጵያ ሕዝብ ተራበ» ብሎ የሚለፍፍና እንደተለመደው በዓለም መድረክ ምግብ የሚለምን መንግሥት ከልመናው ጎን ለጎን ለም የእርሻ መሬት ለውጭ አገሮች ሲቸበችብ መመልከት ግራ ማጋባት ብቻ ሳይሆን ያስደንቃል። ከዚህ የበለጠ «ትራጄዲ» እና «ኮሜዲ» በአንድ ላይ የተዋሃዱበት እውነታ ከየት ይመጣል? እንዴት ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሰው የራሱን አገር መሬት ያለምንም ገደብ ለውጭ አገር ሰው አሳልፎ ይሰጣል? ጉዳዩን የሚከታተሉ የዓለም የምግብ ድርጅት ባለሥልጣን የሆኑ አንድ የውጭ አገር ሰው የመሬት ሽያጩን ሂደትና አፈጻጸም በተመለከተ የታዘቡትን ጋዜጣው እንደሚከተለው ይጠቅሳል፤

> **“These contracts are pretty thin; no safeguards are being introduced. . . . You see statements from ministers where they are promising everything with no controls, no conditions.”**

ጋዜጣው ለአብነት ያህል የሕንድ ኢንቬስተሮች በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ 2.5 ቢሊዮን ዶላር ለኢትዮጵያ እርሻዎቻቸው እንዳዋሉ ይጠቅስና . . .

**China and other Asian countries are also queuing up to buy land. . .**

ብሎ ቁርጣችንን ይነግረናል። የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮችም ቅርጫው ውስጥ እንደገቡ ጋዜጣው ማስታወሱ አልቀረም። ለመሆኑ ከመሬቱ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ወዴት ነው የሚሄደው? የአገሪቱን ገበሬ ለመርዳት ይውል ይሆን? ከውጭ አገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ተቋማት በእርዳታና በብድር የሚገኘውስ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር የገበሬውን ኑሮ ለማሻሻልና የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሳደግ ምን ያህል አስተዋጽኦ እያደረገ ነው? ገንዘቡ በእርግጥ በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ የሚውል ከሆነስ ለምንድነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከረሀብ ነጻ መሆን ያልቻለው? ለምንድነው ኢትዮጵያ በምግብ አቅርቦት ራሷን መቻል እያቃታት ለም መሬቷን የእርሻ መሬት እጥረት ላለባቸው አገሮች አሳልፋ እንድትሰጥ መደረጉ? የራስን ለም መሬት ለውጭ ዜጋ ከመቸርቸር ተቸግሮም ሆነ ተበድሮ የራስን የእርሻ ሀብት ማሳደግና ማስፋፋት ትርፉ በመቶ እጅ አይመዝንም?

በጋዜጣው ሪፖርት መሠረት በሚሊዮኖች ሄክታር የሚገመት ምርጥ መሬት ለ«አግሪቢዝነስ» መድቤአለሁ የሚለው የኢትዮጵያ መንግሥት በአንጻሩ የራሱን አገር ሕዝብ ሰቆቃ የመስማት ፍላጎት ያለው አይመስልም። ጋዜጣው እንዲህ ይለናል ትእይንቱን ሲገልጽልን . . . ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ በሕንዶች ባለቤትነት ከተያዘ ሰፊ የእርሻ ቦታ ላይ ሆነው ሲመለከቱ . . .

**. . . it was possible to see a river designated for irrigating cornfields and rice paddies; it is no longer open for locals to water their cows. Several shiny green tractors bounced across the six-mile long field where teff, the local grain, once grew.**

በገዛ አገሩ የበዩ ተመልካች የሆነው ኢትዮጵያዊ ገበሬ፥ በራሱ አገር ባይተዋር የሆነው ኢትዮጵያዊ፥ ስብዕናውንም ክብሩንም ተገፎ በአዲስ መልክ በተዋቀረና የራሱ መሪዎች በፈቃደኝነት ለውጭ ኃይሎች መሣሪያ ሆነው በሚያካሂዱት ክፉ የቅኝ አገዛዝ ሥርዐት መሬቱን እየተነጠቀ፥ ጉልበቱን እየተበዘበዘ ይገኛል። ረጅምና አኩሪ የነጻነት ታሪክ ባለቤት ለሆነና ነጻነቱን አስከብሮ ለኖረ ሕዝብ ከዚህ የበለጠ ውርደት ይኖር ይሆን?

የውርደታችንን ልክ ለመረዳት ያህል . . . የመሬት ሽያጩን ንግድ ለማስተዋወቅ የተቋቋመ አዲስ የመንግሥት ድርጅት ባልደረባ የሆኑ፥ ኢትዮጵያዊ ስም ያላቸው አንድ ግለሰብ የተናገሩትንና ጋዜጣው ላይ የሰፈረውን ጥቅስ መመልከቱ ይበቃል፤

**"There's no crop that doesn't grow in Ethiopia. . . . Everybody is coming."**

ነውራችን ክብራችን የሆነበት ክፉ ዘመን! አዎ! **"Everybody is coming."** ይህ የሰውዬው አባባል በብርቱ ሊያስጨንቀን ይገባል። ወንጀለኛውንም፥ አፍራሹንም፥ ነውረኛውንም፥ ዘራፊውንም፥ ቀማኛውንም፥ ባሕልና ታሪክ አጥፊውንም፥ ኢትዮጵያዊ ሕጻናትን ሻጩንና ገዳዩንም፥ የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኛውንና አከፋፋዩንም

. . . ሁሉንም . . . በማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ የሚለውንም ጅብ ሳይቀር ኢትዮጵያ ዛሬ በደስታ ታስተናግዳለች . . . ዶላር እስከከፈለ ድረስ። ውርደት በሜትሪክ ቶን የሚለካ ምርት ቢሆን ኖሮ እኛ ኢትዮጵያውያን ባዶ የሆኑትን ጎተራዎቻችንን በአንድ ጊዜ ሙሉ እናደርጋቸው ነበር።

ከጋዜጣው ላይ የመጨረሻ ጥቅስ ልውሰድ፦

> **Desperate for foreign currency, the government of former Marxist rebels who once proclaimed “land to the tiller!” has set aside 6 million acres for agribusiness.**

እውነትም «መሬት ላራሹ!» . . . አሮጌ ቢመስልም አዲሱ መፈክር! በአዲስ «የለውጥ» መንፈስ፣ በአዲስ «ዓለም አቀፋዊ» መልክ የተነደፈ ፕሮግራም።

«መሬት ላራሹ!» . . . የራስን ሕዝብ መሬት የለሽ አድርጎ የውጭ ዜጋን ባለመሬት የሚያደርግ አዲስ ጽንሰ ሀሳብ!

«መሬት ላራሹ!» . . . ኢትዮጵያን የአፍሪካ ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም «የዳቦ ቅርጫት» የሚያደርግ ፕላን . . . በእርግጥ ዳቦውም ሆነ ቅርጫቱ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ንብረት አይደሉም እንጂ!

አዲሱ «መሬት ላራሹ!» . . . የኢትዮጵያን መሬት እየቆራረሰ፣ እየሸነሸነ ለውጭ ባለሀብቶች የሚቸረችር «የልማት» መርሀ ግብር።

ይህ ነበር እንዴ የእነዚያ ተማሪዎችና ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች ዓላማ? የእነዚያ ሰማዕታት ፍላጎት?

«መሬት ላራሹ!» . . . ትርጉሙ የተዛባበት፣ በቅራኔ የተሞላ መፈክር!

እስቲ ለአፍታ እናስበው . . . «የኢትዮጵያን አፈር በጫማችሁ ይዛችሁ መሄድ አትችሉም» ብለው የፈረንጆቹን ጫማና እግር ያሳጠቡ ብርቅ የኢትዮጵያ ልጆች ዐፅም ያረፈበት፣ ለኢትዮጵያ ክብርና ነጻነት እንደ ሻማ የነደዱ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የጀግኖች ኢትዮጵያውያን አጥንት የተከሰከሰበት ክቡር መሬት ዛሬ በዶላር ይቸረቸራል።

የእነዚያ ባለውለታዎቻችን ዐፅም ምን እያለን ይሆን? «አገር አፍራሹ ትውልድ»?!

---

**ቴዎድሮስ አበበ**
Springfield, VA
ኅዳር ፳፩ቀን ፳፻፪ ዓመተ ምሕረት | November 30, 2009